ትዝብት ቁ.16

ነሃሴ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.(25-08-2012)

# እንባ ሳይፈስ ማልቀስ

የኢትዮጵያ ሕዝብ መቼም አልታደለም።የራሱን ስሜት ሳይሆን የመሪዎቹን ከበሬታ በሚያወድሰው የደስታና ሃዘን ትያትር ውስጥ በመገደድ ገብቶ ተዋናይ ከመሆን አላረፈም። መብቱን ለመጠየቅ፣ሃሳቡን ለመግለጽ እንዳይሰበሰብ በተከለከለበት አደባባይ በደርግ ጊዜ የቀበሌ ዕቃ የመግዛት መብቱ እንደማስገደጃ መሳሪያ በመሆን መንግሥት ባዘጋጀው የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ሰልፍ ላይ እንዲገኝ ይገደድ ነበር።አሁን ደግሞ የአምባ ገነኑን የመለስ ዜናዊን ሞት አስመልክቶ በወያኔ የሚመራው የዘረኞች መንግሥት ተብዬ ቡድን ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍና ተቀባይነት እንዳለው ለማስመሰል ከመጮህ በስተቀር ዘለላ እምባ ጠብ የማይላቸው የተገዙ አልቃሾች፣ የስርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ የባለስልጣኑ ቤተሰቦች፣በቀበሌ የተገደዱ ችግረኞችና ሥራ አልባዎች ጥቁር ቱቢት ለብሰው ፎቶ ግራፍ ተሸክመው በአዲስ አበባና በየክፍላተ ሃገሩ ከተማ አደባባይ፣በቀበሌ አዳራሽ ወጥተው እንዲያለቅሱ የመንግሥት ትዕዛዝ ወጥቶ በማየት ላይ ነን። የሚገርመው ነገር ጣራ ቀዶ ከሚወጣው ጩኸት ጋር አንዲት ዘለላ እምባ በሙሾ አውራጆቹ ፊት ላይ ሲፈስ አለመታየቱ ነው።የመንግሥት ሠራተኛም ጥቁር ለብሶ በየመሥሪያቤቱና እንደየደረጃው በቤተመንግሥቱ አዳራሽ እየሄደ የሃዘን መግለጫውንና ለመለስ ዜናዊ አገዛዝና ስርዓት ድጋፉን እንዲሰጥ ተገዷል።የመለስ ሞት እንደታወቀ በሚስጥር ተይዞ ሁኔታው እስኪመቻች ድረስ በብዛት ከውጭ አገር የገባው የጥቁር ልብስና የቱቢት ጣቃ ለወያኔ ነጋዴዎች ሌላ የገቢ ምንጭ ፈጥሮላቸዋል።አንድ ሜትሩ በአስር ብር ይሸጥ የነበረው ሰሞኑን ከአስራአምስት ብር በላይ ሲሆን በየቀኑ ዋጋው እየናረ ነው።በዚህ ብቻም አልቆመም፤መለስ ዜናዊ ለማስመሰል፣ከልቡ ሳይሆን ከአንገት በላይ ላቀደው የአባይ ግድብና ለሌሎቹ የግንባታ ሥራዎች ህዝቡ ገንዘብ እንዲያዋጣ የሚያስገድድ ጥሪ እየተላለፈ ነው።በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይላሉ ይህ ነው።

ወያኔ እንኳንስ በልማት ስም በሞትም ሰበብ ገንዘብ ለመሰብሰብ ሃፍረት የማይሰማው ቀማኛ ቡድን መሆኑን የሰሞኑ አድራጎት ሌላው ማረጋገጫ ነው።

የጠሉት ይወርሳል እንደሚባለው በቴሌቪዥ እንደተመለከትነው የሰሜን ኮሪያ መሪዎች አባትና ልጁ ሲሞቱ ሕዝብ ተገዶ መሬት ለመሬት እየተንከባለለ ሲያለቅስ ጉድ ነው ብለን እንዳልታዘብነው ዛሬ ደግሞ በአገራችን ሲደገም ስናየው እውነትም የአምባ ገነኖች አስተዳደር በህዝቡ ላይ የጣለው ፍርሃትና፣ግዴታ ከሞቱም በኋላ በቀሪ ደጋፊዎቻቸው ጥረት የማይወገድ አባዜ እንደሆነ እንረዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎቹና በመሪዎቹ ቤተሰቦች ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ወጥቶ እንዲያለቅስና ደረቱን እንዲመታ፣ፊቱን እንዲነጭ ሲገደድ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም።የአምባገነኖች ስርዓት እስካለ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል።እርግጥ ነው ሰው

ሲሞት የሚያውቁት አልቅሰው ቢቀብሩት ተገቢ ነው፤ምክንያቱም አብረው ያሳለፉት፣የተጋሩት ደስታና ሃዘን፣ጨዋታና ቁምነገር ከፊት ላይ ድቅን ሲል፣ላያገኙትና የመጨረሻው መለያየት መሆኑ ሲታሰብ ውስጣዊ ስሜትን ይነካል፤ሳያውቁት ከቁጥጥር ውጭ የሆነ እምባ ሊፈስ ይችላል።ይህ አይነቱ ከውስጣዊ ስሜት የመነጨ እውነተኛ ሃዘንና ለቅሶ ነው።

በጎ ነገር ሰርተው፣የሕዝብን መብት አክብረውና አስከብረው፣የአገርን ዳር ድንበር፣ጥቅምና ነጻነት ጠብቀውና አስጠብቀው ለሚያልፉ መሪዎች ከእንባ በላይ ክብር ባለው የታሪክ መዝገብ ውስጥ ሊመዘገቡና ሊወደሱ ይገባል።ለእንደነዚህ አይነቶቹ መሪዎች ኢትዮጵያ ትልቅ ህያው ቦታ ትሰጣቸዋለች።ሕዝቡም አክብሮና አፍቅሮአቸው ከልቡ ያስቀምጣቸዋል።በሙሾና በለቅሶ ሳይሆን በዘፈንና በእንጉርጉሮ ያወድሳቸዋል። መንግስቱ ሃይለማርያምንና መለስን ለመሳሰሉት አምባገነን መሪዎች ግን የሚኖረው የአክብሮትና የፍቅር ውዳሴ ሳይሆን የጥላቻ ትዝታ ነው።ሲሞቱ ነብሳችሁን አይማረው አገሪቱን ሲኦል እንዳደረጋችሁ እናንተንም ሲኦል ያውርዳችሁ እንጂ በገነት ያሳርፋችሁ የሚላቸው የለም።

የአምባገነኑን የጭካኔ ሥራ ግፍና ወንጀል በመሸፋፈን የተለየ ቀለም ለመቀባት የሚሞክሩት ሃይሎች ፣ጥቅማቸውን ያስከበረላቸው የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች በየጎረቤት አገሩ ለሚያካሂዱት የዘረፉ ወረራ ውድ የኢትዮጵያ ልጆችን እየላከ በየጦር ሜዳው እየማገደ የሚያስጨርስላቸው የከበርቴ አገሮች፣በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብትና መሬት ላይ እንደልባቸው እንዲያዙ እድል የተሰጣቸው የውጭ አገር ባለሃብቶችና ቢጤዎቹ አምባገነንና የነጮች ጫማ ላሽ የሆኑ የአፍሪካ መሪዎች ብቻ ናቸው።

የመለስ መሞት ስለዴሞክራሲ መብት፣ስለሰብአዊ መብት፣ስለእኩልነት፣ስለአገር አንድነትና ነጻነት፣ስለፍትህና ሕጋዊ ስርዓት መስፈን የቆሙና የሚታገሉት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም አቀፍ ሃቅና ሰላም ወዳዶችን አያሳዝናቸውም። በኢትዮጵያም ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ የተገደሉባቸው፣በሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦቻቸው በእስራት የሚማቅቁባቸው፣በሚሊዮን የሞቆጠሩ በርሃብና ችነፈር የሚገረፉና በየቀኑ የሚረግፉ ዜጎች፣በሚሊዮን የሚቆጠሩ በየባእድ አገሩ ተሰደው የሚኖሩና የግፍ ክንድ የሚያርፍባቸው ለግላጋ ወጣቶች፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተምረው ሥራ አጥ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የወያኔና የኢሕአዴግ መሪዎችና ስርዓቱ ከመሬት ገጽ ቢጠፉ በደስታ እንባ ያፈሱ ይሆናል እንጂ በሃዘን አይቆራመቱም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተገዶ እንዲያለቅስ፣ተገዶ እንዲደግፍ ሲደረግ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ከዚህ በፊት በታሪክ በተደጋጋሚ የታየ ትያትር ነው።"አገርና ድርሻ" በሚል እረእስ ገና በመጻፍ ላይ ባለሁትና ባልጨረስኩት አነስተኛ የትውስት መጽሃፍ ውስጥ ካሰፈርኩት ከሃምሳ አምስት ዓመት በፊት የስድስት ዓመት ልጅ ሆኜ ትዝ ከሚለኝ ተመሳሳይ ታሪክ ለግንዛቤ ያህል ለማቅረብ ቦታውና ጊዜው አስገድዶኛል።መጽሃፉን በቅርብ ጊዜ ጨርሼ በአንድነት ግንባር ለሚመራ ትግል በማበርከት የገቢ ምንጭ እንዲሆን ሃሳብ አለኝ።ያ ካልሆነም ለኢትዮጵያ ወጣቶች አንዳንድ እቅዶች መደጎሚያ እንዲሆን አበረክተዋለሁ።

ንጉስ ሃይለሥላሴ በሕዝቡ ኑሮና አስተሰሰብ ላይ የነበራቸውን ተጽእኖ በእኔ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚኖረው የሚያውቀው ቢሆንም ለማያውቀው ትውልድ እንዲያውቀው ማድረጉ ተገቢ ነው እላለሁ።ከነዚህም አንዳንዶቹን በመጥቀስ ለማሳየት እሞክራለሁ። በንጉሱ የክብረበዓላት ቀን፣የሚኸጎደጎደውን  ውዳሴና ዝካሬ ትቼ በሃዘን ወቅት የሚኖረውን የሕዝብ ውጣ ውረድ በሚከተለው  እንደሚከተለው ለመሳየት እወዳለሁ፡፤

በ1949 ዓ.ም ልዑል መኮንን የተባሉት ወንድ ልጃቸው ሲሞቱ ምንም እንኳን የስድስት ዓመት እድሜ ውስጥ ብሆንም ትዝ የሚለኝ ነገር አለ።

የንጉሱ ልጅ በ"አደጋ" መሞት እንደታወቀ በተወለድኩበት ደሴ ከተማ ትልቅ የሕዝብ ሃዘን ሆኖ ዋለ፤ደሴ ከተማ ውስጥ በሚገኘው አሁን የቢዝነስ ኮሌጅ በሆነው በታላቅ ወንድማቸው በልዑል አስፋው ወሰን (አልጋወራሽ)ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ ሕዝብ በእድር እየተገደደ ቀኑን ሙሉ ሲያለቅስ፣ደረት ሲመታና ፊት ሲነጭ ዋለ።ከዚያን ቀን ጀምሮ  ለሁለት ወራት ያህል አገሪቱ በነበራት ብቸኛ፣ደካማና አነስተኛ የሬድዮ ስርጭት ከሃዘን መልእክትና ሙዚቃ በስተቀር ምንም አይነት የሚያዝናና ጨዋታም ሆነ ዘፈን አይተላለፍም ነበር።ደግሶ ማግባትና መዳር ባይከለከልም ዘፈንና ጭፈራ ክልክል ነበር።የመንግስት ሰራተኛ በክንዱ ላይ ጥቁር ቱቢት እንዲያስር ወይም ጥቁር ቆብ እንዲያደርግ በትእዛዝ ተገዶ ነበር።

የልዑሉ ስባት ይሁን አርባ ቀን ትዝ አይለኝም ከየጠ/ግዛቱ የሕዝብ ተወካይ የሆኑ የመንግስት ሰራተኞችና የመሬት ባለቤቶች፣ባለርስቶች ወደ አዲስ አበባ ሄደው ንጉሱን ለቅሶ እንዲደርሱ ተገደዱ።ትእዛዙን ያልፈጸመ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚደርስበት ከሥራው ወይም ከርስቱ እንደሚነቀል በማስፈራራት መግለጫ ወጥቶ ከገጠርም ከከተማም እየተውጣጣ ብዙ ሰው ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ነበር።የእኔም እናት መሄድ ነበረባት።በዚያን ጊዜ ጉዞው በጣም አዳጋች ነበር።እንደዛሬው መንገዱ የቀናና የመጓጓዣውም አውቶቡስ ፈጣንና ምቹ አልነበረም። አሁን በስድስት ሰዓት ውስጥ የሚጠቀልሉት አራት መቶ ኪሎ ሜትር በዚያን ጊዜ ከሁለት ቀን በላይ እንዲያውም ሶስት ቀን ይፈጅ ነበር።በዚህ መስመር ላይ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው መጓጓዣ ሃጂ ሃሰን እረሽድ የሚባሉት ነጋዴ ንብረት የሆነ እሱም እንደ አሁኑ ወይም ከሱ በኋላ እንደመጣው የወሎ ፈረስና የአንበሳ አውቶብስ የተመቸ አልነበረም።ጋራጅ ባላቸው ጣሊያኖች የጭነት መኪናው ተቀጥቅጦ ወደ አውቶብስነት የተለወጠ ነበር።ስለሆነም ፍጥነቱም ምቾቱም እንደነገሩ ነበር።

ከየአቅጣጫውና ከየጠቅላይ ግዛቱ የተሰበሰበው ሃዘነተኛ አዲስ አበባ ደርሶ ንጉሱ በተቀመጡበት ሰገነት ፊት ለፊት በየአገሩ ተወካይ መሪዎች እየተመራ ሃዘኑን ከገለጸ በኋላ በተመሳሳይ መጉላላትና ድካም ወደ የመጣበት ሲመለስ የእኔም እናት አብረዋት ከሄዱት ጋር ተመለሰች። እቤት ለነበረውና ላልሄደው ጎረቤት ስለነበረው ሁኔታና ስለለቅሶው ሲናገሩ እንደሰማሁት፤ከየአገሩ የተሰበሰበው ሃዘነተኛ ቁጥር ከመጠን ያለፈ ነበር፤ እንደ ሰልፈኛ በንጉሱ ፊት እያለቀሰና እየጮኸ ማለፉን፤ጭራሽ ሃዘን ሳይሆን የለቅሶ ውድድር ወይም የለቅሶ ህብረትርኢት እንደነበረ ለቀረው ሰው ሲያወጉ ሰምቻለሁ።በዚህም የለቅሶ ውድድር አማራው ደረቱን እየመታ፣ፊቱን እየነጨ፣ዶርዜው እየዘለለና ከመሬት ላይ እየተፈጠፈጠ፣ኦሮሞው በፈረስ ላይ እራሱን በአለንጋ እየገረፈ፣

የሌላውም ከባቢ ህዝብ እንዲሁ እንደየባህሉ ሃዘኑን ሲገልጽ ዋለ።በዚህ ሁሉ የግዳጅ ለቅሶ በፈረስ ሆኖ የለቅሶ ትእይንት በማሳየት ግሩም ድንቅ የተባለው ሰላሌን በመወከል የተገኘው ለቅሶ ደራሽ ነበር።ዋንጫ ቢኖር ኖሮ ተሸላሚ ይሆን ነበር ማለት ነው።በዛም ጊዜ የጥቁር ልብስ ጣቃ፣ጥቁር ቆብና የቱቢት ዋጋ ከመደበኛ ዋጋው ንሮ ነበር።

በተከታዩም ጊዜ በንጉሱ ቤት ሃዘን የደረሰው የንጉሱ ባለቤት የነበሩት ግርማዊት እቴጌ መነን አስፋው በ1954 ዓ.ም. ባረፉ ጊዜ ነው።የዛን ጊዜ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ስለነበርኩ ሁኔታውን በደንብ አውቃለሁ።ከትምህርት ቤት ተሰልፈን፣በክንዳችን ላይ የጥቁር ቱቢት እራፊ አስረን፣ በጥቁር ቱቢት የተለበደ ከካርቶን በልብ ቅርጽ ያዘጋጀነውን በመርፌ ቁልፍ በደረታችን ላይ ለጥፈን በከተማው አደባባይ በለቅሶው ትእይንት ላይ ውለናል። በተለይም እቴጌ መነን ወሎዬ በመሆናቸው የደሴ ከተማ የሃዘን ቤት ሆኖ ነበር የከረመው። እንደተለመደው ለወራት የቆዬ ብሔራዊ ሃዘን ነበር።እንኳንስ በአካል በፎቶግራፍ የማያውቃቸው ደሃ ሕዝብ  በእድር እየተገደደ እየየ እያለ ሲያለቅስ ዋለ። ለቀጣዮቹም ወራት ዘፈን መስማት፣በሰርግ መጨፈር የተከለከለ ነበር። ሌላው የንጉሱ ወንድ ልጃቸው የልዑል ሳህለሥላሤ ሞት በአገር ደረጃ ሃዘን ቢደረግም እንደመጀመሪያው ልጃቸው አልነበረም።እርግጥ ዘፈንና ሙዚቃ ተከልክሎ ነበር።ቀንም ማታም የሚሰማው የሃዘን ሙዚቃ ብቻ ነበር።

ይህንን የገለጽኩት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥርዓቱም ሆነ በባሕሉ አስገዳጅነት ሕዝቡ ሳይመርጣቸው ስልጣን ከያዙ አምባገነኖች ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማሳየት ነው። በሌላው አገርም የነበረውና ያለው  የንጉዋዊና አምባገነናዊ አገዛዝ ቦታው፣ ስልትና መንገዱ ከጊዜ ብዛትና ከድገት አኳያ የተለዬ ቢመስልም በመሰረቱ አንድ አይነት ነው።ከልጅ ልጅ እየተወራረሰ የሚዘልቅ የጉልበተኞችና ያሻጥረኞች ስርዓት ነው።ሃዘን ሲደርስባቸው አገሩ ሁሉ የሃዘኑ ተካፋይ እንዲሆን ይገደዳል፤ ደስታና ፌስታ ሲሆን ግን ሕዝቡ የዛ ተካፋይ አይሆንም።የበይ ተመልካች ነው።አንባገነኖች ህዝባቸው ትዝ የሚላቸው መከራ ሲደርስባቸው ወይም ወራሪ ጠላት ሲመጣባቸውና ከስልጣናቸው ሊያሶግድ የሚችል የተቃዋሚ ሃይል ሲነሳባቸው ድጋፉን እንዲሰጣቸውና ከጎናቸው ኢንዲቆም ብቻ ነው።

አንድ ሃይለኛና ጊዜ ያነሳው ግለሰብ እንዴት ስልጣን ላይ ሊወጣና አልፎ ተርፎም ዘውድ ጭኖ ንጉስ ለመባል እንደሚበቃ፣በሕዝቡ አስተሳሰብና ነጻነት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምን እንደሚመስል በእድሜየ ካየሁት አንዱን አንስቼ ለማሳየት እወዳለሁ። እርግጥ እርዕስ ከሆነው ከኢትዮጵያ ታሪክ ወጣ ቢልም ግንኙነትና መመሳሰል አለው ብዬ አምናለሁ።የትም ሆነ የትም ዘውዳዊና አምባገነናዊ ስርዓት በሂደት አንድ እስከሆነ ድረስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተመሳሳይ የታሪክ ዝምድና ይኖረዋል።

ታሪኩ የተከናወነው በአንዷ የአፍሪካ አገር በሆነችው መካከለኛ አፍሪካ ሬፑብሊክ ውስጥ ነው።ይህች አገር እስከ 1960 የአውሮፓ አቆጣጠር ድረስ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ነበረች።በ1960 ላይ ነጻ ወጥታ በፕሬዚደንት መተዳደር ጀመረች።ምንም እንኳን ለስሙ ነጻ አገር ሆና ባንዲራ ቢውለበለብባትም ከፈረንሳይ መንግስት መዳፍ ስር መሽከርከሯ አልቀረም።ጥቁር ፈረንሳዮች በሆኑ ያገሪቱ ተወላጆች ስትታመስ ኖራለች።በመጨረሻው በኩዴታ ስልጣኑን የያዘው የጥንት የፈረንሳይ ተራ ወታደርና በአገልግሎት የሃምሳ

አለቃና የሻምበል ደረጃ የደረሰው የስልሳ ዘጠኝ ልጆች አባትና የአስራ ሰባት ሴቶች ባል የሆነው ጅን በደል ቦካሳ ነበር። በ1977 እራሱን ንጉስ ብሎ በግራና በቀኝ የክንፍ ምስል በሰፈረበት ሁለት ሽህ ኪሎ በሚመዝን ንጹህ የወርቅ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ከፐርሽያ በተሰራ በእንቁና በአልማዝ የተንቆጠቆጠ ዘውድ ደፋ። የንግስና ስሙንም ናፖሌዎን ብሎ ሰየመ።ለዚህ በዓል የወጣው ወጭ ሃያ ሚሊዮን ዶላር ሲሆን የአገሪቱን ጠቅላላ የዓመት ባጀት አንድ ሶስተኛውን የሚሸፍን ነበር።በበዓሉ ላይ የፈረንሳይ መንግስት የአየር ሃይሉ፣የባህር ሃይሉና የምድር ጦሩን በሰልፍ እንዲሳተፉ አድርጎ ድጋፉን የገለጸ ሲሆን ጠቅላላ ዝግጅቱን የመራውና ያቀነባበረው ፈረንሳዊው አርቲስት ጅን ፒዬ ዱፖ ነበር።ፈረንስዮች ይህን ድጋፍና ትብብር ያደረጉት ካገሪቱ እየጎለጎሉ የሚወስዱት ለኒኩሌር መሳሪያ የሚገለገሉበትን የኡራኔዬም፣ የአልማዝና ወርቅ እንዲሁም ልዩ ልዩ ማእድን ቁፋሮ ዋስትና ለማግኘት ነበር።ይኸው ጉደኛ የሆነው ቦካሳ  ቀደም ሲል ከሊቢያው መሪ ከጋዳፊ ጋር ግንኙነት በማድረጉና እንዲያውም ሃይማኖቱን ለውጦ በመስለም ስሙንም ወደ ሳላህ ኤዲ አህመድ ቦካሳ በመለወጡ ከፈረንሳዮች ጋር ተቃቅሮ ነበር።ከጋዳፊም ጋር የነበረው ወዳጅነት ውሎ አላደረም ተቃቃረና መልሶ ወደ ነበረበት የካቶሊክ እምነት ተለወጠ።ከዚህ በኂላ ነው ንጉስ ለመሆን ምኞትን ፍላጎት ያደረበት።በንጉስነት የሚያባክነው የአገሪቱ ሃብትና የሚፈጽመው በደልና ግፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲወገዝ ፈረንሳዮች ሌላ ካርታ ለመምዘዝ ተገደዱ ።በ1979 ዓ.ም. በፈረንሳዮች ተሳትፎ በኩዴታ ተወግዶ አገሪቱ ወደነበረችበት የፕሬዚደንት አስተዳደር እንድትመለስ ሆነ።ሌላ የፈረንሳዮች ቡችላ የሆነ ሥልጣኑን ተረከበ። ቦካሳም በጎረቤት አገር በአይቮሪኮስት በስደት ከቆየ በኂላ በኦክቶበር 1986 ወደ አገሩ ተመልሶ በሌለበት የተላለፈበት የሞት ቅጣት ፍርድ ወደ እስራት ተቀይሮለት በመጨረሻው ያገሪቱ መሪ ለእስረኛው ሁሉ ምህረት ሲያደርጉ እሱም ተለቆ ትንሽ ከኖረ በኂላ በልብ ድካም በተወለደ በሰባ አምስት ዓመቱ በሞት ተሰናበተ።ከመሞቱ በፊት ይኸው ጉደኛ ሰው መንፈስ ሰፍሮብኛል፣በራዕይ ታይቶኛል፣ አስራ ሶስተኛው የክርስቶስ ሃዋርያ ሁኛለሁ ማለት ጀምሮ ነበር።

ይህ ሰው አገሪቱ መሪ በነበረበት ጊዜ በአገሪቱ የሬድዮ መገናኛ ንግግር በሚያደርግበት ወቅት ንግግሩን ጀምሮ እስኪጨርስ ድረስ ሕዝቡ ከምንም አድራጎት ተቆጥቦ ንግግሩን ቆሞና አንገቱን ደፍቶ እንዲያዳምጥ ንግግሩን ሲያበቃም በጭብጨባና በልልታ እንዲያሳርግ ይገደድ ነበር፤ያንን ያልፈጸመ ወይም የጣሰ አይቀጡ ቅጣት ይደርስበት ነበር።የቦካሳን ታሪክ ያነሳሁት ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የንጉስን አነሳስና የአምባገነኖችን ምግባር ለማሳየት ነበር።

አሁን ባለንበት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ዓለም የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሳለች፣ የዴሞክራሲ ስርዓት ሰፍኗል፣በሚባልበት ጊዜ አገራችንና ሕዝባችን ሲገፉ የኖረውን ልማድና በመሪዎች ግዴታ የማይፈልገውን እንዲያደርግ ፣የሚጠላውን እንዲወድ፣ የሚወደውን እንዲጠላ የማድረጉ ነገር ይኸው በመለስ ዜናዊ ሞት ዙሪያ አገርሽቶበት ይታያል።የውስጥና የውጭ ተባባሪዎች ሕዝቡን ግራ እያጋቡና እየከፋፈሉ የያዙትን የጥቅም ማስጠበቂያ ስልጣን ላለመልቀቅ ሰፊ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ናቸው።

መለስና የሚመራው ቡድን ወንጀለኛ መሆኑ ሲታወቅ ለፍርድ መቅረብ ሲገባው ከፈጣሪ በታች ያለ፣ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ አድርጎ ለማቅረብ መሞከር

ሕዝቡን አላዋቂ ማድረግና መናቅ ነው።መለስ ይመራው የነበረው ቡድንና የቆመለት ሥርዓት የዘራፊዎች፣የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ ለማጫረስ የተዋቀረ፣ለውጭ አገር ጥቅም የቆመ፣በአፍሪካ መሬት ላይ ቅኝ ገዢዎች ተክለው የሄዱት የከፋፍለህ ግዛ ስልትና  የዘር ፖለቲካ  መልሶ እንዲያብብ የረዳ፣ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካ ጠር የሆነ መሪ ነው። አሁን በአገር ውስጥና በውጭ አገር መንግስታት የሚካሄደው ሽርጉድ የነበረው ጸረ አንድነት ስርዓት ሳይናጋ ለመቀጠል የሚቻልበትን መንገድ በመፈለጉ ላይ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የሚፈርስበትንና የተሻለ ስርዓት የሚሰፍንበትን ጊዜና ዕድል በጉጉት ይጠብቃል።በተቃዋሚ ድርጅቶችም ላይ ተስፋውን ጥሎ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።እነዚህ ተስፋ የተጣለባቸው የተለያዩ ድርጅቶች ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግና የህዝቡን ፍላጎትና ጥያቄ ለመመለስ አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።የአንድነት ግንባር ፈጥረው የአገራቸውና የህዝባቸው ጋሻና መከታ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል።መብትና ድርሻቸውን በልመና ሳይሆን በትግልና በግድ የሚያገኙት  መሆኑን ማሳየት ይኖርባቸዋል።እውስጥ ካሉት እውነተኛ አገር ወዳድና ዴሞክራቲክ ሃይሎች ጋር ግንኙነት መፍጠርና ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ አስቸኳይ ውሳኔ ላይ መድረስ አለባቸው።በአደባባይ የሚታየው የተገደዱና የተገዙ ግለሰቦች የሚያወርዱት ሙሾና መፈክር አቋማቸውን ሊያለሳልሰው አይገባም። ዛሬ አልቃሽ ሆኖ ሙሾ የሚያወርደው የተገደደ ህዝብ ነገ ደግሞ ስርዓቱ ሲገረስስ ጉሮ ወሸባይ እያለ የሚጨፍር ይሆናል።

ከመደምደሜ በፊት ቀደም ሲል ከጻፍኳቸው ግጥሞች አንዱን ለማቅረብ እወዳለሁ።

## አገር እንደ ዳቦ

አገር እንደ ዳቦ እየተቆረሰ፣

ከሰላ ተበልቶ ጅቡቲ ደረሰ፣

ጅቡቲ ተበልቶ ኤርትራ ደረሰ፣

ኤርትራ ተበልቶ ወልቃይት ደረሰ፣

በወልቃይት በኩል ጉምዝን ተሻግሮ ጋምቤላ ደረሰ፣

ለጎራሽ(ለጠላት) እንዲያመች እየተገመሰ።

አገር እንደ ዳቦ እየተቆረሰ፣

ዳር ዳሩ ተበልቶ መሃል ተደረሰ።

ይኽ ተላላኪ እንግዳ አስተናጋጅ እየተጣደፈ፣

ኢትዮጵያን ለማጥፋት

እየሸነሸነ አገር ለማስበላት፣

በክልል፣በጎሳ ቆራሽ አሰለፈ።

የውጭ ወራሪ ሌላ መንገድ ቢያጣ፣

አገሩን ለመያዝ(ለመግዛት) መለስ ብሎ መጣ።

ከሰሃራ በታች ከሱዳን ባሻገር፣

ከኬንያ ወዲህ በኢትዮጵያ ድንበር፣

መሬትና ቦታ መግዛት ካማራችሁ፣

እርካሽ ነጋዴ ኢህአዴግ(መለስ) አለላችሁ።

ጣልያንና እንግሊዝ ከአምሳ ዓመት በኋላ ከኢትዮጵያ በወጡ፣

ኢህአዴግን ፈጥረው እንደገና መጡ፣

በዲሞክራሲ ስም ከፋፍለው ሊግጡ።

በርካሽ ሸምተው በውድ ሊሸጡ፣

ያገር ውስጥ ነጋዴ መድረሻ ሊያሳጡ።

በስመ ፈላሻ፣በስመ ሎተሪ ሕዝብን እያሶጡ፣

መለስ ቀለስ ብለው ለመበተን መጡ።

ጥንትም ሰሜኑ ነው መግቢያና መውጫቸው፣

ወደ መሃል አገር መረማመጃቸው።

ኢራን፣ ሕንድ፣ ቻይና፣ ቱርክና እሩስያ፣

አውሮፓ አሜሪካ፣ሳውዲና ሊቢያ፣

በቅርጫው ገብተዋል በነጻው ገበያ፣

ወግድ ባይ በሌላት በኢትዮጵያ።

ያገሬ ደሃ ሕዝብ አትቀበላቸው፣

ከልማት ባሻገር ሌላ ግብ አላቸው።

ለውስጡ ተነፍጋ ለውጭ የቀረበች፣

እየተገመሰች፣እዬተቆረሰች፣

ኢትዮጵያ አገራችን ክብ ዳቦ ሆነች፣

በዚህ ከቀጠለ ሙልሙል ትሆናለች።

ያለም ነጋዴዎች ካለፈው ተማሩ፣

ሕዝብ ስልጣን ሲይዝ በባዶ እንዳትቀሩ፣

ከወያኔ ጋራ አትፈራረሙ አትደራደሩ፣

የሱ ብቻ አይደለም የሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብ ነው አገሩ።

አገሬ አዲስ

ነሃሴ 2002 ዓ.ም. (ሴፕቴምበር 2010)